# ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ በ36ኛው የኢሕአፓ በዓል ላይ በመገኘት ያስተላለፉት መልእክት

## የዴሞክራሲያዊ ለውጥ ትግል

ኢሕአፓ 36ኛውን ዓመት እያከበረ ነው፡፡ እኔም በዚህ ዓመት በዓል ላይ በመገኘቴ ደስታዬን እገልጻለሁ፡፡ የዴሞክራሲ ለውጥ ለማምጣት ያላቋረጥከው ወንዝ፥ ያልወጣኸው ተራራ፥ ያላፈሰስከው ደም የለም፡፡ አንተን ለማጥፋት የተሰማወሙ ይመሰል፤ ባንድ በኩል ደርግ፥ በሌላ በኩል ሻዕቢያና ወያኔ ጦርነት ከፍተውብሃል፡፡ ለዴሞክራሲ ለውጥ መታገልህና የከፈልከው መስዋእት በማያጠራጥር መንገድ የታሪክ ምስክር ነው፡፡ ይህንም ሐቅ ጠላቶችህ በይፋ ባይቀበሉትም በውስጣቸው እንደማይክዱት አያጠራጥርም፡፡ እንደሌሎቹ የአድር ባይ ጠባይ ቢኖርህ ኖሮ 36 ኛውን ዓመት ባላከበርክ ነበር፡፡ በዓመት በዓልህ ተገኝቼ እንኳን ለ36ኛው ዓመት አደረሰህ አላለሁ፡፡

በግለሰብ ደረጃ ከመካከላችን፥ ስለ አገራችን ኢትዮጵያ ውስብስብ ችግሮች መፍትሔ አለኝ የሚል የለም፥ ሊኖርም አይችልም፡፡ መፍትሔ የሚገኘው በነፃ መንገድ ከሚደረግ የጋራ ውይይት ብቻ ነው፡፡ አለበለዚያ ሐቁና መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉት ተቀብረው ይኖራሉ፡፡ እኛም ሐቆቹና መፍትሔዎቹ ተሰውረውብን የተደናበረ ኑሮ ለመኖር እንገደዳለን፡፡ መፍተሔዎቹ ካልተገኙ ደግሞ ጥፋቶቻችንን ስንደጋግም እንኖራለን፡፡ ነፃ ውይይት ሐቅንና መፍትሔን ይወልዳል፡፡ በዚህም ምክንያት የተነሳ ነው ቶማስ ጀፈርሰን ከነፃ ጋዜጣና ከመንግሥት አንዱን ምረጥ ቢሉኝ ነፃ ጋዜጣን እመርጣለሁ ያለው፡፡ በእውነቱ አባባሉ ትልቅና ገንቢ ሀሳብ ያዘለ ነው፡፡ የመለሰ ዜናዊ መንግሥት ነፃ ውይይት እንዳይስፋፋ ለማገድ ያልወሰደው እርምጃ የለም፡፡ ምክንያቱ ግልጽ ነው፡፡ ነፃ ውይይት ሐቅንና መፍትሔን ስለሚወልድና፤ ሐቅና መፍትሔ ደግሞ በይዘታቸው የመለሰና የግብረ አበሮቹን ወንጀሎች ማጋለጣቸው የማያቀር በመሆኑ ነው፡፡

በአገራችን በኢትዮጵያ ያለው አደጋና ውዥንብር ሁላችንም የምናውቀው ይመስለኛል፡፡ ኢሳያስንና መለስን ደጋግመን መኮነኑ ሳይሰለቸንም አልቀረም፡፡ እስቲ የዴሞክራሲ ለውጥ የምንፈልግ ከተቃዋሚ ክፍል ነን የምንል፥ ስለራሳችን በነፃ መንገድ እንወያይ ፡፡ ወደ ፊት መጓዝ ምኞታችንና ፍላጎታችን ከሆነ፥ እስካሁን ያልቻልንበት ምክንያት ምንድ ነው ብለን ስለራሳችን መወያየት አለብን፡፡ ስለ ኢሳያስና ስለ መለሰ ማውራት የቀለለንን ያህል፥ ስለራሳችን መወያያት ሳይከብደን የቀረ አይመስለም፡፡ በእኔ በኩል ሁለት ነጥቦችን በማንሳት ሀሳቤን እንዳካፍል ይፈቀድልኝ፡፡

አንደኛው የወያኔን ስነ ፍጥረትን የሚመለከት ነው፡፡ በተቃዋሚ ክፍል መሀል በዚህ ጥያቄ ላይ መናጋትን የፈጠረ ትልቅ ውዥንብር ያለ ይመስለኛል፡፡ ተቃዋሚ ድርጅቶች ለመለሰ መንግሥት የሰላምና የሀገራዊ እርቅ ጥሪ ሲያቀርቡ ይገርመኛል፡፡ የባሰ ደግሞ፥ ከግንቦት 1997 ምርጫ በኋላም ጥሪውን የሚደጋግሙ አሉ፡፡ በእውነቱ የሚገርም ብቻ ሳይሆን የሚያሳዝንም ነው፡፡ በኔ በኩል ቀሪን ገረመው ሳልል አልቀረሁም፡፡ ወያኔ ሥልጣን ሳይጨብጥ ጀምሮ ሀገራዊ የሆነ የሰላምና የእርቅ ጥሪን ይቀበላል ብዬ ጨርሼ አምኜም አላውቅም፡፡ ይቀበላል ብሎ ማመንም ጨለማውን እንደብርሃን፥ ቀጣፊውን እንደ ሐቀኛ ፥አምባገነኑን እንደ ዴሞክራት አድርጎ እንደ መውሰድ ይሆናል፡፡ በተፈጥሮው ወያኔ የዴሞክራሲ መንፈስ ኖሮት አያውቅም ሊኖረውም አይችልም ከአፈጣጠሩ ጀምሮ የወያኔ ፍልስፍና አንድ ነው፡፡

ይህም

“ ተገልበጥ ተገለባበጥ

ዋና ግብህ ሥልጣን ጨብጦ ለመሰንበት"

የሚለው ነው:: አንዳንድ የታሪክ ምሳሌዎቸን እየጠቀስኩ ልቀጥል::

ደርግ ፀረ ዴሞክራሲ ነው፥ የትግራይ የብሔረሰብ እኩልነት መብት ይከበር፥ ብሎ ተደራጅቶ ሲን ቀሳቀስ ፤ ከትግራይ መሬት ለቃችሁ ውጡ በሚል መፈክር በኢሕአፓ ላይ አምባገነናዊ በሆነ መንገ ድ ጦርነት አወጀ:: በትግሬ ጠባብነት ተነሳስቶ የሥልጣን ቀዳዳ ሲያይ ፥ በሰፊው ኢትዮጵያ ሊነግ ሥ ወሰነ:: አዲስ አበባ እንደገባ፥ የአማራው ክፍል ተለጣፊ ድርጅት ስላልነበረው፥ ለተወሰነ ዓመታ ት በኢትዮጵያ ስም ሲታገል የቆየውን ኢህዴንን በድንገት ወደ አመራው የፖሊተካ ድርጅት ቀየረ ው:: እዚህ ላይ የሚያስገርም ካለ የወያኔ አሰራር ሳይሆን የኢሕአዴን መሪዎች መቀበላቸው ነው:: ወያኔ አዲስ አበባ ሲገባ የአክራሪውን "የኮሙኒስት" መፈክር ሲያሰማ ፥ ሳያውል ሳያድር ግን፥ ብል ጣ ብልጡ መለሰ ዜናዊ የአፍሪካው ቀንድ ሙሻረፍ ሆኖ ብቅ አለ:: የብሔረሰቦችን መብት የሚያከ ብር ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ አውያለሁ እያለን የብሔረሰብ እኩልነት ጥያቄን ለማፈን የወሰደ ው እርምጃ የኦነግ መሪዎች በወቅቱ ያያዙትን የመንግሥት ሥልጣን ጥለው ስደት እስከመሄድ አስ ገደዳቸው:: የውጭ ጌቶቹን ለማስደሰትና ዴሞክራሲያዊ ለመምሰል፥ ውሱን የሆነ ምርጫ እንዲደረ ግ ቢፈቅድም የምርጫው ውጤት ሲያስፈራው የተራውን ሕዝብ ደም አፍሰሰሰ::

በማያሻማ መንገድ፥ መለሰና ግብረ አበሮቹ የሚያምኑት

"ተገልበጥ ተገለባበጥ

ዋና ግብህ ሥልጣን ይዞ ለመሰንበት"

የሚለው ነው:: ይህን የመሰለ የፖለቲካ ፍልስፍና የሚከተል ድርጅት ሀገራዊ የሆነ የሰላምና የእር ቀ ጥሪ ይቀበላል ማለት ህልም ነው:: ፓርላማ እየተሳተፍን በሰላም መንገድ ወያን እናጋለጠዋለን እ ንዲሁም ሰላማዊና ነፃ በሆነ ምርጫ ከሥልጣን እናወርደዋለን የሚሉ የተቃዋሚ ድርጅቶች የወያኔ ሥነ ፍጥረት ጨርሶ የገባቸው አይመስልም::

ሌላ እንኳ ቢቀር ከግንቦት 97 ምርጫ ታሪክ መማር እንዴት ይሳናቸዋል? :: በተግባራቸው የመለሰ ን አገዛዝ እንደሚያራዝሙ መገንዘብ ይኖርባቸዋል:: በታሪክም ሳይጠየቁ አይቀሩም::

ሁለተኛው ነጥቤ የኅብረት ጥያቄ የሚመለከት ነው:: ኅብረት ማለት ምንድ ነው? ኅብረተስ ከማን ጋ ር? ለምንስ? በተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል የኅብረት ጥያቄን አስመለክቶ ውዥንብር ላይ አለ:: ም ንም እንኳን መፈክራቸው "መጀመሪያ ኅብረት በኋላ ውድድር" ቢልም ውድድሩን፥ ሽኩቻውን፥ ሲ ያስቀድሙ ነው የቆዩት:: በእኔ አስተያየት ኅብረት ሲባል በመሠረቱ ተቃዋሚ ነኝ የሚለውን ሁሉ ማቀፍ አይደለም:: የአይዶሎጂ ፥ ድርጅት አስላለፈን ይጠይቃል:: በቁጥራቸው እጅግ የተወሰኑና ፖሊሲያቸው ከፋፋይ የሆነና፥ በዘር መልክ የተደራጁትን በኅብረት ስም ማቀፍ፥ በመሠረቱ የተሳሳ ተ መንገድ ነው:: የእነ በየነ ጴጥሮስን፥ የመራራ ጉዲናን፥ የአረጋዊ በርሄን፥ በቅርብ ደግሞ እንዳየነ ው የገብሩ አስራት ድርጅቶችን ብንወሰድ ሁሉም የኢትዮጵያ የዴሞክራሲዊ አንድነትን እንቀባላለን ይላሉ:: ብልጥነት ካልሆነ በስተቀር ለምን በኢትዮጵያ መልክ እንደማይደራጁ የሚገርም ነው:: እን ደነዚህ ዓይነት ድርጅቶችን በኅብረት ከማቀፍ ይልቅ ከመጀመሪያው ሳይውል ሳያድር መጋፈጥ ያስ ፈልጋል:: ዛሬም ሆነ ነገ ለተወሳሰብ ሀገራዊ ችግሮች ዋና ምንጭ መሆናቸው አይቀርምና:: ሌላው እኩል ነን ብለው በሚያምኑ ድርጅቶች መሃል ፥ ኅብረት ጨርሶ ሊመሠረት አይችልም:: ከኅብረቱ ይልቅ ውደድሩና ችኩቻው ነው የሚቀድመው:: ለ17 ዓመታትም በይፋ ታይቷል::

ኅብረት ለመፍጠር እራሱን ያጠናከረ አንድ ድርጅት ብቅ እንዲል ያስፈልጋል፡፡ ጠንካራው ድርጅ ት ሌሎቹን ሲያሰባስብና ሲመራ ብቻ ነው ጠንካራ ኅብረት ሊመሠረት የሚቻለው፡፡

የተቃዋሚ ድርጅቶችን ታሪክ ስከታተል ብዙ ዓመታት አሳልፌያለሁ፡፡ ይህን የታሪክ ሚና ሊጫወት እድል ያለው ድርጅት ኢሕአፓ ብቻ ይመስለኛል፡፡ ይህንንም የታሪክ ሐቅ በመረዳት ይመስለኛል ደርግ÷ መኢሶን÷ ሻዕቢያና ወያኔም ኢሕአፓን ለማጥፋት የዘመቱት፡፡ ባሁኑ ወቅትም ኢሕአፓ ሀገ ር ቤት ገብቶ የሰላሙን ትግል እንዳያራምድ ወያኔ የሚያጨናግፈው ይህንኑ በመፍራት ነው ፡፡ ወያ ኔ ስለኢሕአፓ ያለው ፖሊሲ የወያኔን ድክመትንና ስጋትን ነው የሚያሳየው፡፡ እንደ ተቀዋሚ ድር ጅት ኢሕአፓ የቆየ ታሪክ ያለው ነው፡፡ ያለ ማወላወል ለኢትዮጵያ አንድነትና ለዴሞክራሲ ሲታገ ል ይኸው 36 ኛውን ዓመት እያከበረ ነው፡፡ በሁለገብ መንገድ የዴሞክራሲያን ትግል ሲያራምድ የቆ የ ድርጅት ነው፡ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለዴሞክራሲያ ለውጥ ያካሄደውን ትግል ሊክድ የ ሚችል ካለ ራሱን የሚያታልል ብቻ ነው፡፡

የሚበዙት ተቃዋሚ ድርጅቶች ትላንትና የተወለዱ ናቸው፡፡ የመሪዎቻቸው የጀርባ ታርክ የሚያጠ ራጥር ነው፡፡ አንዳንድ በዘር÷ የከፋፋይነትን ፖሊሲ በማንገብ የተደራጁ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ በዘር አይዶሎጂ ሲንቀሳቀሱ ሰንብተው በጉዟቸው ላይ ፖሊሲያቸውን ቀይረው ለመላው ኢትዮጵያና ለዴ ሞክራሲያ እንታገላለን ያሉ ናቸው፡፡ ሎሎቹም አሁን ለዴሞክራሲ እንታገላለን ይበሉ እንጅ ከደርግ ወይም ከወያኔ ጋራ ሆነው የኢሕአፓን የዴሞክራሲ ትግል ሲያጨናግፉ የቆዩ ናቸው፡፡ ሌሎችም የ ድርጅት መሪዎች ከመለሰ ይበልጥ እስከመገንጠል የሚለውን አንቀጽ 39ኝን በሥራ ላይ ለማዋል የ ቆረጡ ናቸው፡፡ አንዳንድ መሪዎች በሀሳብ ሳይስማሙ በቀሩ ቁጥር ያቋቋሙትን ኅብረት ጥለው የሚ ወጡ÷ የሚታገሉ ድርጅቶችን የሚክዱ ፍጥረቶች ናቸው፡፡

በተለያየ መንገድ ብናየው÷ ኢሕአፓ ብቻ ነው ሊያሰባስብና ሊመራ የሚችለው፡፡ በዚህ ላይ መከራ ከርም አያስፈልግም፡፡ መጠያቅ ያለብን ኢሕአፓ ይኸን የታሪክ ሚና ሊጫወት ተዘጋጅቷል ወይ? የሚለውን ነው፡፡ ለ17 ዓመታት ኢሕአፓ አሰሱን ገሠሡን በኅብርት ስም ለማሰባሰብ ያልሞከረው መንገድ የለም፡፡ በውጭ ታዛቢነት ምን ያህል የገንዘብና የሰው ኃይል እንደባከነ ሳልገምት አልቀረሁ ም፡፡ ድርጅቶች ነን የሚሉትን ሁሉ እየጋበዘ÷ እያስተናገደ ÷ እያቋቋመ ወደ ማብቂያው ላይ ሲሸኝ በይፋ ታዝበናል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ግልጽ በሆነ መንገድ እያስተናገዱ የመሸኘቱ ሥራ በራሱ ውስጣ ዊ ሎጂክ አብቅቷል፡፡ በኔም በኩል ማብቃት አለበት እላለሁ፡፡ አሁን የቀረው የኢሕአፓ አማራጭ የ ራሱን ድርጅት ማጠናከር ነው፡፡ በኔ በኩል ኢሕአፓ ሌላ አማራጭ የለውም፡፡ ታሪኩንና ስሙን ሊጠ ብቅ ከፈለገ፡፡ ይህንንም መልአክት እንደሚረዳው ተሰፋ አለኝ፡፡

ንግግሬን ልደምድም

ኢሕአፓ ሆይ! የታሪክ እድል አንተን ብቻ በመምረጥ÷ እጇን ዘርግታ ልታቅፍ ቆማለች፡፡ እድልህን አታባክን በኔ ይሁንብህ÷ ለብዙ ዓመታት ታሪክህን ስከታተል ቆይቻለሁ፡፡ እራስህን አጠናክረህ ትግ ሉን ቀጥል፡፡ ያን ጊዜ እንኳን የሚደግፍህ ቀርቶ÷ ከአንጀታቸውም የሚጠሉህ አንተን ለመከተል ላ ይና ታች መሯሯጣቸው አይቀርም፡፡

ደግሜ እንኳን ለ36 ኛው ዓመት አደረሰህ እላለሁ፡፡

EthioLion.org